# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር 21-31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታና ግምገማ እንዲሁም

## ከጃንዋሪ 1-10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2023
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
| --- | --- |


እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ....... 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....... 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ....... 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....... 4

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ....... 5

በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 5

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 6

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ....... 7

ሁኔታ አዝማሚያ ....... 7

ካርታ 6 ከዲሴምበር 21-31 የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ ....... 7

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 8

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 8


## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በዲሴምበር ወር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅና ፀሐያማ የነበሩ ቢሆንም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አልፎ አልፎ በጥቂት ቦታዎች ዝናብ ከማግኘታቸው በስተቀር አብዛኛውን ጊዜ ደመናማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በወሩ መጨረሻ ጥቂት ቀናት ለዝናብ መፈጠር መንሰኤ የሆኑት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር በማሣየታቸው የደመናው ሽፋን በሰሜናዊው የሀገሪቱ ሥፍራዎች በመስፋፋቱ በበጋ ወቅት ዝናብ በማያገኙት በጥቂት ቦታዎች ላይ ዝናብ ዘንቧል። በመሆኑም በአንዳንድ የደቡብ ምዕራብና የሰሜን አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። ለመጥቀስም ያህል በማጀቴ 66.3 እና 34.1 እና በካቺሴ 46.8፣ በአይራ 30.6 እና 30.4 ሚ.ሜ. ዝናብ ተመዝግቧል። በሌላ በኩል በአንዳንድ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የአየር ሙቀት ከ5 ዲግሪ ሲልሸየስ በታች ተመዝግቦ ነበር። ለመጥቀስም ያህል በሀሮማያ 2.4፣ በደባርቅ 4.7 እና 4.5፣ በአርሲ ሮቤ 4.0 እና 4.5፣ በዳንግላ 4.0፣ በባሌ ሮቤ 4.6 እንዲሁም በወገል ጤና 4.0 በዲግሪ ሲልሸየስ ተመዝግቧል።


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከአማራ የሰሜን፣ መካከለኛውና የደቡብ ጎንደር፣ የዋግህምራ፣ ባቲ፣ የሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በሁሉም የወለጋ፣ በሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ በአርሲና በቡኖ በደሌ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል በአኙዋክና መጃንግ ፤ ከአፋር በዱብቲና በሰመራ ጣቢያዎች፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም በአብዛኛው የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች ላይ ከ5-100 ሚሜ የሚደርስ ከ2-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ የሰሜን፣ መካከለኛውና የደቡብ ጎንደር፣ የዋግህምራ፣ ባቲ፣ የሰሜንና ደቡብ ወሎዞኖች፤ ከኦሮሚያ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ በአርሲና በቡኖ በደሌ ዞኖች፤ ከአፋር በዱብቲና በሰመራ ጣቢያዎች፤ ከጋምቤላ ክልል በአኙዋክና መጃንግ ዞኖች፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም በአብዛኛው የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የወቅቱን ዝናብ ማግኘት የሚገባቸው የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎችን ጨምሮ ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1    ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የዲሴምበር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት የነበረው አየር ሁኔታ በዚህ ወቅት ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ፡ በሌላ በኩል በደቡብና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመጠን አነስተኛም ቢሆን የተስተዋለው እርጥበታማ ሁኔታ በተለይም የበጋን ወቅት እንደ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ለሚጠቀሙ አካባቢዎች ለሚያከናዉኑት የግብርና እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታ ነበረዉ፡፡ በተጨማሪም ይህ ሁኔታ በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት  አዎንታዊ ጎን ነበረው፡፡ ይሁን እንጂ በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት የበጋ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ባልሆኑት ሰሜናዊው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ  አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸው፡፡ (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የዲሴምበር መጨረሻዎቹ ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ያመዘነ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጥቂት ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ከነዚህም መካከል በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛዉ ባሮ አኮቦ፣ በላይኛው ተከዜ፣ በመካከለኛውና ምስራቃዊ አባይ፣ በጥቂት መካከለኛው አዋሽ ኪስ ቦታዎች እንዲሁም በላይኛው ዋቤ ሸበሌ እና ገናሌ አካፋይ ቦታዎች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች በአብዛኛው ቦታዎቻቸው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሆነው ቆይተው ነበር (ካርታ 5) ፡፡


ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት  በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ  ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡  ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ መካከለኛው፣ ምስራቅና የደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ የሌሊቱ እና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል ይጠበቃል። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ምክንያት በጥቂት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የደመና ሽፋን እና አነስተኛ የዝናብ መጠን ያለው ዝናብሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚቀጥል ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል ከኦሮሚያ ቄለም ወለጋ ፣ ምስራቅ ሸዋ፣ አርሲ፣ ባሌ እና ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች ፤ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ እና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ ምዕራብ ትግራይ፤ ከአፋር ክልል ዞን 3፣ 4 እና 5፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀድያና ሀላባ ዞኖች፤ ከምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የሸካ ዞን፤ ድሬዳዋ፣ ከሶማሌ ክልል የሲቲ ዞን በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ ከአነስተኛ እሰከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ። የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ ሆነው ይቆያሉ።




ካርታ 6    ከጃንዋሪ 1-11/2023 የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በጃንዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት ደረቃማው የአየር ሁኔታ የሚዘወተር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሰብል ስብሰባው ተጠናቅቆ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት በስፋት የሚስተዋልበት ወቅት ነው፡፡ በሌላ በኩል ከደረቃማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የበጋው ወቅት የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በቀጣይነት የሚስተዋልበት ጊዜ ነው፡፡ በጃንዋሪ የመጀመሪያዎቹ ቀናት የሚጠበቀው ደረቃማው የአየር ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩም ከደረቃማውና ከነፋሻማው አየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ በቀጣይነት ሊኖር የሚችለው ቅዝቃዜ በተወሰኑ ቦታዎች እድገታቸውን ሙሉ በሙሉ ባልጨረሱ ሰብሎች፣ እንዲሁም በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው ይችላል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች እንደ አካባቢው ሁኔታ የሚኖረውን ቅዝቃዜ ለማሻሻል የሚረዱ የተለመዱ ተግባራትን ለማከናወን የበኩላቸውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራሉ፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በተለይም በሰሜን ምእራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በመካከለኛዉ በተወሰኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት ከማሻሻል አንፃር ጥሩ ጎን ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ አስር ቀናት የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በአሞ ጊቤ፣ በላይኛው ባሮ አኮቦ፣ በላይኛው ገናሌ እና በዋቢሸበሌ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጠበታማ እንደሚያገኙ ትንበያው ይጠቁማል። በተቀሩት ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡ የበጋው ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በወንዞች፣ በግድቦችና በኩሬዎች እንዲሁም በከርሰምድር ውስጥ ያለው ውሃ መጠን ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ስለሚያሳድር የውሃ መጠን ቀስ በቀስ እየቀነሰ ይሄዳል።